የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.50
ADDIS ABABA 25th May, 2020

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፺፯/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በጅማ - ጭዳ እና ሶዶ - ሳውላ የመንገድ ፕሮጀክት (ጅማ-ጭዳ ክፍል) ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጃፓን ዓለም አቀፍ የትብብር ኤጀንሲ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……ገጽ ፲፪ሺ፭፻፶፫

## Content

Proclamation No.1197/2020

Japan International Co-operation Agency Loan Agreement for financing Jimma-Chida and Sodo-Sawla Road Upgrading Project (Jimma-Chida Section) Ratification Proclamation.......Page 12,553

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፺፯/፪ሺ፲፪

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጃፓን ዓለም አቀፍ የትብብር ኤጀንሲ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለጅማ - ጭዳ እና ሶዶ - ሳውላ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፱ ቢሊዮን ፮፻፶፭ ሚሊዮን የጃፓን የን (ዘጠኝ ቢሊዮን ስድስት መቶ ሃምሳ አምስት ሚሊዮን የጃፓን የን) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጃፓን ዓለም አቀፍ የትብብር ኤጀንሲ መካከል መጋቢት ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1197/2020

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE JAPAN INTERNATIONAL CO-OPERATION AGENCY

WHEREAS, a Loan Agreement, between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Japan International Co-operation Agency stipulating that the Japan International Co-operation Agency provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 9,655,000,000 Japanese Yen (Nine Billion Six Hundred Fifty Five Million Japanese Yen) for financing Jimma-Chida and Sodo-Sawla Road Upgrading Project (Jimma-Chida Section) was signed in Addis Ababa on 30th day of March 2020;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 5th day of May, 2020;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በጅማ - ጭዳ እና ሶዶ - ሳውላ የመንገድ ፕሮጀክት (ጅማ-ጭዳ ክፍል) ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጃፓን ዓለም አቀፍ የትብብር ኤጀንሲ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፺፯ /፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Japan International Co-operation Agency Loan Agreement for financing Jimma-Chida and Sodo-Sawla Road Upgrading Project (Jimma-Chida Section) Ratification Proclamation No. **1197**/2020".

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጃፓን ዓለም አቀፍ የትብብር ኤጀንሲ መካከል መጋቢት ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር ET-P4 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement Number ET-P4 signed in Addis Ababa on 30th day of March, 2020 between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Japan International Co-operation Agency is hereby ratified.

## ፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፱ ቢሊዮን ፮፻፶፭ ሚሊዮን የጃፓን የን (ዘጠኝ ቢሊዮን ስድስት መቶ ሃምሳ አምስት ሚሊዮን የጃፓን የን) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## 3. Power of the Ministry of Finance

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 9,655,000,000 Japanese Yen (Nine Billion Six Hundred Fifty Five Million Japanese Yen) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the *Federal Negarit Gazettee*.

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**Done at Addis Ababa, on this 25th day of May, 2020**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**